# *የካህሳይ ኩርባዎች*

## *ክፍል አንድ*

### *በሽጋው ሙሉማር 12-24-15*

### *እንደ መንደርደሪያ...*

ይህ ፅሁፍ በ2005 ዓ.ም በካህሳይ አብርሃ ተፅፎ ለንባብ የበቃውን፤ "የአሲምባ ፍቅር" የተሰኘውን ታሪካዊ መፅሃፍ በወፍ በረር የሚዳስሳ ነው፡፡ የመፅሃፉ ደራሲ በአሲምባ በነበረው የኢትዮጵያ ህዝባዊ አብዮታዊ ሰራዊት ወይም ኢህአሰ በተባለው የኢህአፓ ወታደራዊ ክንፍ ውስጥ የነበረ ታጋይ ነው፡፡ ከተራ ታጋይነት እስከ ሃይል መሪነት በቆየባቸው ጥቂት አመታት፤ በአሲምባ ውስጥ ያሳለፈውን ውጣ ውረድ፤ የትግልና የፍቅር ህይዎት የሚዳስስ፤ እውነተኛ ታሪክ ነው፡፡

ታሪኩ ከተከናወነ ከ30 አመታት በኋላ ለንባብ የበቃው "የአሲምባ ፍቅር" ያ ትውልድ የወጣ የወረደበትን፤ ሀገርና ህዝብ ለሚባል እውነት የተከፈለውን መስዋዕትነት፤ የነበረውን የአላማ ፅናት፣ ፍቅርና ትግል በሚገባ ያሳያል፡፡ አዲሱ ትውልድ ስለ ኢህአፓ ምንነትና ማንነት፤ በአጭር ጊዜ ስሙ ገኖ፤ በአጭር ጊዜ ለምን እንደተበተነ፤ ፍንጭ ይሰጣል ብዬ አምናለሁ፡፡

ባለቅኔው ሎሬት ፀጋዬ ገብረ መድህን "የሰው ልጅ አንድም ከፊደል ሀ ብሎ፤ አንድም ከመከራ መዝገብ ዋ ብሎ ይማራል፡፡" እንዳሉት ያ ትውልድ በርሃብና በእርዛት፤ በመከራና በጦርት ለዚህ ትውልድ ልዕልና ዋጋ ከፍሏል፡፡ በእኔ እምነት ይህ ትውልድ ወይም አዲሱ የሚባለው ትውልድ፤ ከዚህ ዘመን ትውልድ፤ አንድም ከሊቅ አፍ፤ ሁለትም ከመፅፍ ያገኘው እውቀት በቂ ነው ብዬ አላስብም፡፡

ደራሲ፣ ገጣሚና ጋዜጠኛ ነብይ መኮንን በመፅሀፉ ጀርባ በሰጠው አስተያየት "የካህሳይ ኩርባዎች ወላጆቹ፤ ከሱ ጋር ነፍስ የተቀባበለው ይመር ንጉሴ የተባለው ገበሬና አሲምባ የወለዳት ድላይ የተባለች ጓድ- ፍቅረኛው ናቸው፡፡" ይላል፡፡ ስለዚህ የካህሳይን ኩርባዎች አንድም ከመፅሀፉና ከደራሲው ጋር ከነበረኝ ቆይታ፤ ሁለትም ከአንዳንድ ታሪካዊ መፃህፍትና ተዛማች ሁነቶች ጋር እያዛመድሁ፤ የወፍ በረር ቅኝቴን አቀርባለሁ፡፡

## ድህረ-ታሪክ

በኢትዮጵያ ህዝቦች የትግል ታሪክ ውስጥ፤ በየጊዜው ሲቀሰቀስ የነበረው አመፅ በ1930ዎቹ ይበልጥ ተጠናክሮ ወጣ፡፡ በተለይ በጎጃም፣ በወሎ፣ በባሌና በትግራይ… በነበረው የገበሬዎች አመፅ ተስፍፍቶ፤ በተለያየ ጊዜና ዘመን ህዝቡ በስርዐቱ ላይ ተቃውሞውን ሲያሰማ ነበር፡፡

ለዘመናት ውስጥ ውስጡን ሲንፈቀፈቅ የነበረው ህዝባዊ አብዮት ነፍስ የዘራው፤ በወርሃ ታህሳስ፤ 1953 ዓ.ም ነበር፡፡ በገርማሜ ንዋይና በመንግስቱ ንዋይ አማካኝነት የተጠነሰሰው የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ፤ በወጉ የተደራጀና የተቀናጀ ባለመሆኑ ሳይወለድ የሞተ ነበር፡፡ አንዳንድ የፖለቲካ ተንታኞች ሙከራውን “በግብታዊነትና በስሜት የተደረገ ነበር፡ ፡” ይላሉ፡፡ ያም ሆኖ ግን በዘመኑ የነበረውን አስተሳሰብ በመቀየር ረገድ ትልቅ ፋይዳ ነበረው፡፡ ምክንያቱም “ሰማይ አይታረስ፤ ንጉስ አይከሰስ፤” በሚል ልማዳዊ አስተሳሰብ ተቀይዶ፤ ብሶቱን በሆዱ ይዞ የኖረው ህዝብ፤ በከቸፈው የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ‘ይህም አለ ለካ!’ እንዲል አስችሎታል፡፡

ራሳቸውን ከሰለሞናዊ የዘር ግንድ ጋር ያስተሳሰሩትና “ሥዩመ እግዚያብሔር ነኝ፡፡” በማለት ለ43 አመታት ያህል ሃገሪቱን ያስተዳደሩት አፄ ኃይለ ስላሴ፤ ከየአቅጣጫው የተነሳውን አመፅ መቋቋም አልቻሉም፡፡ ችግሩን ለማርገብ የተለያዩ ማሻሻያዎችን ቢያደርጉም፤ የንግስና ዘመናቸውን ግን ማራዘም አልቻሉም፡፡ በዚህም የሃገሪቱ የመጨረሻው ንጉሰ ነገስት በመሆን ስልጣናቸውን ለቀቁ፡፡

በወቅቱ ከተለያዩ ወታደራዊ ክፍሎች የተውጣጡ ጥቂት መስመስዊ መኮንኖች፤ ለዘመናት ውስጥ ውስጡን ሲንተከተክ የኖረውን ህዝባዊ አመፅ መከታ አድርገው፤ በአቋራጭ መንበረ ስልጣኑን ተቆጣጠሩት፡፡

ስልጣኑን የተቆጣጠሩት መኮንኖች፤ ራሳቸውን ጊዚያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ብለው በመሰየም፤ ሀገሪቱን ማስተዳደር ጀመሩ፡፡ ደርግ ከመነሻው “ያለ ምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም!” ብሎ ቢነሳም፤ የህዝቡን የዘመናት ጥያቄ መመለስ ግን አልቻለም፡፡ ምክንያቱም የህዝቡን የለውጥ ፍላጎት መሰረት አድርጎ ወደ ስልጣን ቢመጣም፤ ሀገሪቱን ለማስተዳደር የሚችል ቅድመ ዝግጅት አልነበረውም፡፡ በዚህ ሳቢያም ህዝባዊ አመፁ ማገርሸት ጀመረ፡፡

'ከድጡ ወደ ማጡ!' እንዲሉ የህዝቡ ኑሮና ሮሮ እያየለ ሄደ፡፡ በዚህ ሳቢያም የህዝቡን ጥያቄ ለመመለስ በርካታ የፖለቲካ ድርጅቶች እንደ እንጉዳይ መፍላት ጀመሩ፡፡ ከእነዚህ የፖለቲካ ሀይሎች መካከል ስሙና ዝናው የናኘው፣ በርካታ አባላትን በአጭር ጊዜ በማፍራት ጎልቶ የወጣው፣ የኢትዮጵያ ህዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ወይም ኢህአፓ ነበር፡፡

ኢህአፓ በገጠር የተራዘመ የትጥቅ ትግል በማካሄድ ወታደራዊውን መንግስት ከስልጣን ለማውረድ የኢትዮጵያ ህዝባዊ አብዮታዊ ሰራዊት ወይም ኢህአሰ የተሰኘ ወታደራዊ ክንፍ መሰረተ፡፡ ሰራዊቱንም በትግራይ አሲምባ፣ በጎንደር፣ በበለሳና በጠለምት አካባቢ ስልጠና በመስጠት የትጥቅ ትግል ጀመረ፡፡ ይሁንና በውስጡ በተፈጠረው ልዩነት ሳቢያ እየተፈረካከሰ ሄዶ፣ ህልውናው መክሰም ጀመረ፡፡

እነሆ አመታት አለፉ… ነገሮች ሁሉ ባልተጠበቀ ፍጥነት ተለዋወጡ፡፡ ስርአቱን ለመገርሰስ በገጠር የተራዘመ የትጥቅ ትግል የጀመሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ህዝባዊ ወያነ ሃርነት ትግራይና (ህወሃት) የኢትዮጵያ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ኢህዴን) በ1980 ዓ.ም አጋማሽ ጥምረት ፈጠሩ፡፡ የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር ወይም ኢህአዴግ የተባለው ጥምረት፣ ወታደራዊውን ስርአት በወርሃ ግንቦት፣ በ1983 ዓ.ም አስወገደ፡፡ ደርግ ለ17 አመታት የነገሰበትን ዙፋንም ተረከበ፡፡

እነሆ አሁንም አመታት ነጎዱ… ነገር ግን በአንድ ወቅት ከሊቅ እስከ ደቂቅ የተከተሉት፣ ገናናነቱ የተመሰከረለት፣ "ጥቁሩ ቮልሸቪክ" እየተባለ የተሞካሸውን፣ የኢህአፓ ትክክለኛ ታሪክ ለትውልዱ በሚገባ ተላልፏል ለማለት ያዳግታል፡፡ ምክንያቱም በዚያ የታሪክ ሂደት ውስጥ ያለፉት ታጋዮች፣ ከስሜት በፀዳ መልኩ የኢህአፓን በሃገሪቱ ፖለቲካ ውስጥ የነበረው ሚና፣ እድገትና ለውድቀቱ መንስኤ የነበሩ ታሪኮች እርስ በእርሳቸው የሚጣረሱ ናቸው፡፡ በዚህ ሳቢያ የአሁኑ ትውልድ ያለፈውን እውነተኛ የኢህአፓ ታሪክ እምብዛም አያውቀውም፡፡ ቢያውቀውም እንኳን በዘመነ ኢህአፓ ያለቀውን አንድ ትውልድ ነው፡፡ ለውድቀቱ ተጠያቂ የሚያደርገው ድርጅቱን እንጅ፣ በሀገሪቱ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ የነበረውን ጉልህ ድርሻ አይደለም፡፡

ስለዚህ የኢህአፓን የውድቀት መንስኤ በሚገባ ለመረዳት፣ በወቅቱ የነበሩ ባለ ታሪኮች ታሪኩን በሚገባ ሊነግሩን ግድ ነው፡፡ ያም ሆኖ ግን ኢህአፓ በኢትዮጵያ ህዝቦች የትግል ታሪክ ውስጥ ጉልህ ሚና የተጫወተ፣ በሃገሪቱ ለተፈጠረው የፖለቲካ ለውጥ መሰረት የጣለ መሆኑ አይካድም፡፡

እንደ አለመታደል ሆኖ ብዙዎቹ የሀገራችን የታሪክ ድርሳናት የተፃፉት በራሳችን ሰዎችና በባለ ታሪኮች አይደለም፡፡ ይህ ባለመሆኑም ያለፈው ትውልድ ለህዝቦች ልዕልና የከፈለው መስዋዕትነት በዘመን ብዛት እየደበዘዘ ነው፡፡ ትውልዱም በራሱ ታሪክ ከመኩራት ይልቅ፤ ታሪክ ያለው ታሪክ አልባ እየሆነ ነው፡፡ ለዚያም ይመስለኛል የራሱን ጀግኖች ዘንግቶ፤ የሆሊውድና የቦሊውድ የፊልም ተዋናዮችን ታሪክ ነጋሪ የሆነው፡፡

ይህ ለምን ሆነ? ካልን ባለ ታሪኮቻችን የኢህአፓን ታሪክ በወጉ ለትውልድ ባለማስተላለፋቸው ነው እላለሁ፡፡ ያ ማለት ግን ስለ ኢህአፓ አነሳስና ውድቀት በባለ ታሪኮች የተፃፉ መፃህፍት የሉም ማለት አይደለም፡፡ ለአብነት ያህል የኢህአፓ አመራር የነበረው ክፍሉ ታደሰ "ያ ትውልድ" በሚል ርዕስ ስለ ኢህአፓ በሶስት ቅፆች፤ በኢህአፓ ወታደራዊ ክንፍ ውስጥ የነበረው አስማማው ሃይሉ (አያ ሻረው) የኢህአሰን ታሪክ በሁለት ቅፅ፤ በህይዎት ተፈራ የተፃፈው "tower in the sky"፣ የመኮንን ገብረ ዝጊ "ፍቅር በዘመነ ሽብር"ና ሌሎችም... ይጠቀሳሉ፡፡

በ2005 ዓ.ም በደራሲ ካህሳይ አብርሃ የተፃፈው "የአሲምባ ፍቅር" ደግሞ፤ በድርጅቱ ውስጥ የነበረውን እውነት ከራሱ እይታና ገጠመኝ በመነሳት ነው የፃፈው፡፡ አንድ ታሪክ በባለ ታሪኩ መፃፉ ደግሞ አንድም ታማኝነቱ፤ ሁለትም ያለፈበትን እውነት ለመረዳት ያስችላል፡፡ በዚህ ሀሳብ ላይ ደራሲ፣ ገጣሚና ጋዜጠኛ ነብይ መኮንን በመፅሃፉ ጀርባ የሰጠው አስተያየት ይጠቀሳል፡፡

"እስካሁን ካነበብኳቸው በኢህአፓ ላይ ያተኮሩ፤ በተለይ በአማርኛ ከተፃፉት መፅሃፍት መካከል፤ የካህሳይን መፅሃፍ ለይቸ ወድጀዋለሁ፡፡ ቀና ነው፡፡ በህፃን የየዋህነት ቀለም የተፃፈ ነው፡፡ ስለ ራሱ ለራሱ ለመንገር ብሎ እንጅ ለሌሎች ለመንገር ብሎ የፃፈው አይመስልም፡፡ ፅሁፉ ያን ዘመን እንደገና ከሌሎች ጋር እንድወያይበት አድርጎኛል፡፡"

## *የካህሳይ ኩርባዎች እንድ- ወላጆቹ*

ደራሲ ካህሳይ ተወልዶ ያደገው በቀድሞው ትግራይ ጠቅላይ ግዛት፤ በአጋሜ አውራጃ፤ ዛላ አንበሳ ወረዳ በምትገኘው ጥርቀ በተባለች የገጠር መንደር ነው፡፡ የቤተ ክህነት ትምህርቱን እስከ ቅዳሴ የዘለቀው ካህሳይ፤ የአርሶ አደር ቤተሰቦቹን እንግልት እያየ ነው ያደገው፡፡ ባደገበት ቀዬ አንዱ ያጣ የነጣ፤ ሌላው ደግሞ መሬትና ምርት የተትረፈረፈው የመሆኑ ምስጢር በለጋ አእምሮው ይመላለስ ነበር፡፡

በአንድ ማለዳ ወላጅ አባቱ ወደ አንድ ባላባት ቤት ይዘውት ይሄዳሉ፡፡ በጓሮው በር ተደብቆ የመጣው ባላባት አርሶ አደር አይመስልም፡፡ ረጅምና ወፍራም፤ ወዘናው የሚያብረቀርቅ ነው፡፡ አባቱ ለባላባቱ ሸሽገው ገንዘብ ሲሰጡት ያያል፡፡ በሁኔታው የተገረመው ብላቴና አባቱን ይጠይቃቸዋል፡፡

“ዳኛ ስለሆነ፤ እኔ የምፈልገውን እንዲያደርግልኝ ነው፡፡” ግራ በመጋባት አባቴን ዐይን ዐይኑን አየሁት፡፡

“እዚህ ሀገር ለዳኛ ገንዘብ ካልሰጠህ ምንም ነገር ማድረግ አትችልም፡፡ ስለዚህ ሁላችንም ጉቦ እየሰጠን ነው የምንኖረው፡፡” አለኝ አባቴ ጉዳዩ እንዲገባኝ፡፡

“ሁሉም ሰው ጉቦ የሚሰጥ ከሆነ ዳኛው ለየትኛው ያግዛል?” አልኩት፡፡

“የሚፈርደውማ የበለጠ ገንዘብ ለሰጠው ነው፡፡” አለኝና “አየህ? የምሰጠው ወድጄ እንዳይመስልህ፤ ይፈርድብኝና ያለኝን አጣለሁ ብዬ ከመፍራት ነው እንጅ፤ ለእርሱ የምሰጠውን ገንዘብ ለአንተ ልብስ መግዣ ባደርገው በጣም ደስ ይለኝ ነበር፡፡ እንዲህ ካላደረግሁ ግን መሬቴን እነጠቅና የጠላት መጫወቻ እሆናለሁ፡፡” ብሎ አስረዳኝ፤ (የአሲምባ ፍቅር ገፅ 31)

ወቅቱ ባለጉልበቶች የሚኖሩበት፤ የዳርዊን አመክንዮ ሃያሉ የሚያሸንፍበት (survival of the fittest) የሚተገበርበት ነበር፡፡ እናም ካህሳይ ይህ በአንድ ሀገር ልጆች ያለው የህይዎት እንቆቅልሽ ግራ እያጋባው ነበር ያደገው፡፡

በአካባቢው ከስድስተኛ ክፍል በላይ ትምህርት ቤት ባለመኖሩ፤ የጀመረውን ዘመናዊ ትምህርት ለመቀጠል ወደ አዲግራት ከተማ አቀና፡፡ በ1964 ዓ.ም የስምንተኛ ክፍል ተማሪ በነበረበት ወቅት ደግሞ፤ የሃገሪቱ የፖለቲካ ትኩሳት ውስጥ ውስጡን የሚብላላበት፤ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በየስርቻው ስለፖለቲካ የሚወያዩበት አመት ነበር፡፡ አንድ ቀን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ትምህርታቸውን አቋርጠው፤ የንጉሱን ስርዐት በመቃወም አመፅ ወጡ፡፡ ወታደሮች ተኩስ ከፈቱ፤ ከተማዋ በተኩስ እሩምታና በተማሪዎች ጩኸት ተናወጠች፡፡

“እኔና የትምህርት ቤት ጓደኞቹ በተፈጠረው ረብሻ ግራ ተጋብተን በድንጋጤ መሸሽ ጀመርን፡፡ ኢትዮጵያ ሆቴል አጠገብ ጨረቃ ቤት የሚባል ነበረ፡፡ እየሮጥን ገባንና

በየአልጋው ስር ተደበቅን፡፡ ወታደሮች በየቤቱና በየቡና ቤቱ እየገቡ ሲፈትሹ፣ እኛንም ከተደበቅንበት እየጎተቱ አወጡን፡፡ ወታደሮቹ ትናንሾቹን ወደ ቤታችን እንድንሄድ ሲለቁን፣ ትላልቆቹን ግን እየደበደቡ፣ እገፈተሩና እየጎተቱ መኪና ላይ ጭነው፣ ወደ እስር ቤት ወሰዷቸው፡፡" (የአሲምባ ፍቅር ገፅ 29)

ይህ በመፅሃፉ የተገለፀው እውነት ወደ ኋላ ላይ ለተቀጣጣለው ህዝባዊ አብዮት እርሾ ነበር፡፡ በህዝቡ ውስጥ የነበረው የለውጥ እርሾ አይሎ የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች በስፋት መንቀሳቀስ ጀመሩ፡፡ የህዝቡን የዘመናት ብሶትና ጥያቄ ያነገበው ኢህአፓ ደግሞ በወጣቱና በምሁራን ዘንድ ተቀባይነት ነበረው፡፡

በለጋ ዕድሜው፣ በቀዬው የሚኖሩ አርሶ አደሮችንና የቤተሰቦቹን የህይዎትና የኑሮ ልዩነት እያዬ ያደገው ደራሲው፣ የወቅቱን የፖለቲካ ትኩሳት ከነባራዊ ሁኔታው ጋር እንዲያገናዝብ እድል ፈጠረለት፡፡ እናም ለተበደለው ህዝብ ጠበቃ ለመሆን ትምህርቱን አቋረጠ፡፡ የህይዎት ኩርባዎቹ ከቤተሰቦቹና ከትምህርቱ ነጠለው፡፡ ኢህአፓን ለመቀላቀል ወደ አሲምባ በረሃ አቀና፡፡

"መስከረም 27 ቀን 1968 ዓ.ም እኔና ታደሰ አፅብሃ በድቅድቁ ጨለማ ከዛላ አንበሳ ተነስተን፣ ኢህአፓዎች ይገኙበታል ወደ ተባለው መነኩሲቶ አቅጣጫ መንገድ ጀመርን፡፡ ስንሄድ አድረን ረፋድ ላይ መነኩሲቶ ደረስን፡፡" (የአሲምባ ፍቅር፣ ገፅ 35)

ብዕርና ወረቀት የያዙ ጣቶቹ ወታደራዊውን የደርግ መንግስት በመጣል፣ የህዝቡን የዘመናት ጥያቄ ለመመለስ የጠበንጃ ቃታ ላይ አረፉ፡፡ ሁሉም ከድል በኋላ ይደርሳል፡፡

ካህሳይ አንደ ዘመኑ ወጣቶች ወደ ሰራዊቱ ሲቀላቀል አብሮት የተጓዘው ጓደኛው ታደሰ አፅብሃ ነበር፡፡ ታደሰ ግን ምክንያቱን ሳይነግረው ከትግሉ ጎራ ሳይደርስ ይመለሳል፡፡ ከደራሲው ጋር በነበረኝ ቆይታ ሁኔታውን አጫውቶኝ ነበር፡፡

"የወጣነው ለትግል ነበር፡፡ ግን ታደሰ ተመለሰ፡፡ እኔ አሲምባ ገባሁ፡፡ ትግሉን ከተቀላቀልሁ ከጥቂት ጊዜ በኋላ፣ ለአንድ ግዳጅ ስንቀሳቀስ አገኘሁት ነበር፡፡ ታደሰ ትግሉን ባለ መቀላቀሉ እንዳዘነና እንደ ተፀፀተ ነገረኝ፡፡ በዚሁ ተለያየን፡፡"

ከአመታት በኋላ ግን ለአንድ ህዝባዊ አላማ ወደ አሲምባ በረሃ አብሮት ሊወጣ የነበረው ታደሰ፣ የአምባገነኑ ወታደራዊ ስርአት ጋሻ ጃግሬ እንደ ነበር መስማቱን ሲነግረኝ እያዘነ

ነበር፡፡ ያ ዘመን ዕርስ በዕርስ መተማመን ያልነበረበት፤ አሳዛኝ ክስተቶች የታዩበት፤ ፈታኝ ጊዜ እንደ ነበር ለመረዳት አያስቸግርም ነበር፡፡

*የካህሳይ ኩርባዎች ሁለት- አሲምባ*

የካህሳይ ሁለተኛው የህይዎት ኩርባ የሚጀምረው አሲምባ በረሃ እንደ ገባ ነበር፡፡ በድርጅቱ መመሪያ መሰረት ቤሰቦቹ ያወጡለትን ስም ቀየረ፤ ካህሳይ መባሉ ቀርቶ አማኑኤል ተባለ፡፡ ምክያቱም በአካባቢው የነበሩት የደርግ የደህንነት ሰዎች ቤተሰቦቻቸውን እንዳያንገላቷቸውና እንዳይታወቁ ነበር፡፡ (ከዚህ በኋላ አማኤል ወይም ደራሲው እያልሁ እቀጥላለሁ፡፡)

አማኑኤል ዛሬም ከአመታት በኋላ ሲያስበው ስሜቱን የሚነሽጠው የድርጅቱ ቃለ መሃላ እንደሆነ ይናገራል፡፡

"እኔ ለሀገሬና ለኢትዮጵያ ህዝብ እስከ መጨረሻው ለመስዋዕትነት ተዘጋጅቸና በኢትዮጵያ አቢዮታዊ ሰራዊት ስር ሁኘ፤ የኢትዮጵያ ህዝብ ነፃ እስኪወጣ እስከ ህይወቴ ፍፃሜ ድረስ፤ በትግል ጎዳና እጓዛለሁ!" የሚል ነበር፡፡ (የአሲምባ ፍቅር፤ ገፅ 44)

"...የሚገርምህ?... አሲምባ እንደ ገባሁ የኢህአሰ ሰራዊት ለመሆን የምንገባው ቃል ኪዳን ነበር፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ቃል ስገባ የተሰማኝ ስሜት ዛሬም ድረስ አለ፡፡ እስካሁን ድረስ ባለው ዘመኔ እንደዚያ አይነት ስሜት ተሰምቶኝ አያውቅም፡፡" ይላል፡፡

ያ ትውልድ ላነገበው አላማ በፅናት እንዲቆም የሚያደርግ፤ የኢትጵያን ህዝብ በደልና ሰቆቃ፤ የፍህና የነፃነት እጦቱን ለመታደግ፤ አንድያ ህይወታቸውን ቤዛ አድርገው፤ የነፃነት ሻማ ለመለኮስ ሲነሱ፤ ዘመናትን ተሻግሮ በእዝነ ህሊናቸው የሚመላለስ ቃለ መሀላ ነበር፡፡

"...ያኔ የህዝብ አደራ ስትቀበል፤ ህዝባዊ አደራ ሲጣልብህ አስበው?..." ሲል መልሶ ጠየቀኝ፡፡ አይን አይኑን ከማየት በቀር መልስ አልነበረኝም፡፡ ከ35 አመታት በኋላ ቃለ መሃላውን አነበነበልኝ፡፡ ስሜቱ ደፈረሰ፡፡ ከአሲምባ ጎንደር፣ ጠለምት፣ ወሎና እብናት ሲጓዝ ያሳለፈውን የህይዎት ውጣ ውረድ፤ ድልና ሽንፈት፤ መማረክና መስዋዕትነት ለአፍታ በእዝነ ልቡናው ሲላወስ፤ እንባው እንዳይወርድ አይኑን አስሬ ያርገበግባል፡፡ ሀዘኑ ቢጋባኝም ያስሜት ፈንቅሎት ሊወጣ ሲታገለው ሳይ ገረመኝ፡፡ ምክያቱም እሱ እድለኛ ሁኖ ያለፈውን ትውልድ የታሪክ አሻራ ለመዘከር በቅቷልና፡፡

ያ ትውልድ በዛሬው ትውልድ አይን ሲታይ ብዙ መልኮች፣ ብዙ ወጎች አሉት፡፡ አንድም በወጉ ተደርዘው የቀረቡ የታሪክ ድርሳናት አለመኖር፣ ሁለትም በተለያየ መልኩ በሀገራችን ታሪክ ውስጥ ጥቁር ትዝታ ያጠላበት፣ በደፈናው አንድ ትውልድ የተቀጠፈበት እየተባለ ስለሚወጋም ይመስለኛል፡፡ ምንም እንኳን የደርጉ ምክትል ፕሬዚዳንት የነበሩት፣ ኮሎኔል ፍስሃ ደስታ በ2008 ዓ.ም ባሳተሙት "አቢዮቱና ትዝታዬ" በተባለው መፅሃፍ ይህን እውነት

"…አንድ ትውልድ የሚለው አይገባኝም፡፡ ስምንት ሺህ አካባቢ እንደሆነ የልዩ አቃቤ ህግ የክስ መዝገብ ያስረዳል፡፡ እኔ የማምነው ይሄን መረጃ ነው፡፡ ምክንያቱም የልዩ አቃቤ ህግ ያረጋገጠው ስለሆነ…" ሲሉ ባይስማሙበትም፡፡

ወቅቱ የህዝቡን የዘመናት ሰቆቃ አንገፍግፏቸው፣ ወደ በረሃ ለትጥቅ ትግል የወጡት ወጣቶች፣ መከራቸው የበዛ እንደ ነበር፣ የያኔው አማኑኤል የአሁኑ ካህሳይ በግልፅ ቋንቋ ማስፈሩን ግን አደንቃለሁ፡፡ እርግጥ ነው በስራ ምክንያት ስንቀሳቀስ ያገኘኋቸውና በተለያዩ ድርጅቶች ውስጥ ተሰልፈው የነበሩ ታጋዮች፣ የዚያ ዘመን ትውስታቸው ከዚህ የተለየ እንዳልሆነ አጫውተውኛል፡፡

ለአብነት የኢህዴን ብአዴን ታጋዮች ይጠቀሳሉ፡፡ የበለሳ አርሶ አደሮች አባ ፈረደ (ጥቁሩ ቮልሸቪክ)፣ አርባ ፀጓሩ አባ ንጋቱ፣ የጉሃላዋ እናት ወይዘሮ አስረበብ፣ የአበርገሌዎቹ ታደሰ ምሩፅና መኮነን ገብርዬ (ጨርግድ)፣ የአርማጭሆወቹ ታጋይ ሻምበል ፀሃይና ታጋይ ይቻላልና የድርጅቱ መስራችና ነባር ታጋዮችም ሆኑ ሌሎች ኢህአፓን ቀድመው የተቀላቀሉ ታጋዮች ለዚህ እውነት ህያው ምስክር ናቸውና፡፡

"የአሲምባ ፍቅር" ደራሲ የያኔው የኢህአሰ አባል ካህሳይ በድርጅቱ ውስጥ የነበሩ እውነተኛ ታሪኮቸችን በመፅሃፍ መልኩ ማቅረቡና የተለየ የታሪክ አንጓ የያዘ በመሆኑ የተለየ ሁኖብኛል፡፡ ሳምንት እንመለስበታለን…

# ***<u>የካህሳይ ኩርባዎች</u>***

***ክፍል ሁለት***

***በሽጋው ሙሉማር***

አንባቢዎቸ እንደምን ሰነበታችሁ? ባለፈው እትም በአሲምባ በነበረው የኢህአፓ የሰራዊት ክንፍ አባል የነበረው ደራሲ ካህሳይ አብርሃ፤ በ2005 ዓ.ም ያሰተመውን “የአሲምባ ፍቅር” የተሰኘውን መፅሃፍና ከደራሲው ጋር የነበረኝን ቆይታ መሰረት አድርጌ በክፍል አንድ በወፍ በረር ማስቃኘቴ ይታወሳል፡፡ ዛሬም የካህሳይ ኩርባዎችን ቅኝት ቀጥያለሁ፡፡ መልካም ንባብ…

የነበረው ስርአት በህዝብ ላይ የሚያደርሰው መከራ አንገሽግሿቸው፤ ነፍጥ አንስተው ለህዝብ ልዕልና በርሃ የወጡት ታጋዮች፤ አንድያ ህይወታቸውን ቤዛ ሊያደርጉ ሲነሱ፤ የሚተኙበት አበባ ምንጣፍ፤ የጣፈጠ ምግብ፤ የሚጠቱትና ንፅህናቸውን የሚጠብቁበት ንፁህ ውሃ ማግኘት የሚታሰብ አልነበረም፡፡ ምክንያቱም የትጥቅ ትግሉ አንድ መራር

ገፅታ የምግብ፣ የውሃና የአልባሳት ችግር ነበረና፡፡ ለዚህ ማሳያ የሚሆነው ደግሞ ደራሲው በትግል ጅማሬው ያስተዋለው እውነታ ነበር፡፡

"ከትውውቁ በኋላ ምግብ ቀረበልኝ፡፡ የገበሬ ልጅ በመሆኔ የምግቡ ዓይነትም ሆነ አቀራረቡ የፈጠረብኝ ስሜት አልነበረም፡፡ ለእኔ ያንን ቡድን መቀላቀል የፈጠረብኝ ስሜት ከምንም በላይ ነበር፡፡ ኢትዮጵያን ለመታደግ ከቆመ ድርጅት ጋር መሰለፌ የፈጠረብኝ መንፈሳዊ ኩራት አጥለቅልቆኛል፡፡"

"አዘውትረን የምንበላው በጋለ ድንጋይ (በቃዬላ) ላይ የሚጋገር ቂጣ..." ነበር፡፡ (የአሲምባ ፍቅር) ገፅ 40ና ገፅ 59፡፡

ለህዝብ እውነት ሲባዝኑ ላያቸው ላይ የፈላውን ቅማል፤ የወረደባቸውን የበረዶ ዝናብ፤ ያለፉበትን ውርጭና ሃሩር ማስታወስ ግን ለዚህ ትውልድ ትርጉም ይኖረዋል፡፡ ምክንያቱም ያለፈው ትውልድ የመከራ ቀንበራቸውን ሰብረው፤ አሁን ላለው ሰላም የከፈሉት መስዋዕትነት ነበር፡፡ ቢሆንም ግን ያለፉበት የመከራ ዘመን ነገም በትውልዱ ቅብብሎሽ፤ ከዘመን ዘመን ይሸጋገር ዘንድ፤ ያለፈውን እውነት በውል ሊውቀው ይገባል ብዬ አስባለሁ፡፡

ይህን የምለው በዘመናዊነትና በቴክኖሎጅ እድገትና ተፅዕኖ ሳቢያ አሻግሮ የሚያማትረው ትውልድ፤ ስለ ሆሊውድና ቦሊውድ ተዋንያኖች፤ ስለ አለማቀፍ እግር ኳስ ተጫዋቾችና ስለ ሌሎች ታዋቂ ሰዎች አፋሽ አጎንባሽ መሆን የለበትም፡፡ እንደ ኢህዴኗ ታጋይ ታሪክ ፈንቴ፤ እንደ ህውሃቷ ታጋይ ማርታ፤ እንደ ኢህአሰዋ ታጋይ ድላይና ሌሎችም ጀግኖቻችን በፊልም ሳይሆን በገሃድ መስዋዕትነት የከፈሉ አያሌ ኢትዮጵያዊ ጀግኖችቻችን ማንነት፤ ከነሻኪራ፣ ከነአንጀሊና ጁሊ፣ ከጀነፈር ሎፔዝና ከሌሎችም በላይ ያደንቋቸው፣ ያከብሯቸው ዘንድ፤ የተሰውለትን አላማ ዘመን ያሻግሩ ዘንድ፤ ገድላቸው እንዲህ በመፅሃፍ ሊዘከር ይገባዋል፤ ቢቻል በፊልምም፡፡

ለዚህ ነው በ"አሲምባ ፍቅር" መፅሃፍ ውስጥ የተሳሉት ባለ ታሪኮች ከራስ ፀጉራቸው እስከ ቁምጣቸው፤ የሰፈረባቸውን ቅማል በተራ ሲቀማመሉ እንደ ነበር፤ ደራሲው እንደ ወረደ ነው የፃፈው፡፡ ለአብነት ታጋይ ጓዶችን በመቅመል የሚደሰተው ፀጋዬ ገብረ መድህ ወይም በትግል ስሙ ፀጋዬ ደብተራው ይጠቀሳል፡፡

"...ፀጋዬ ግለኝነት የማያጠቃው፣ ከራሱ ይልቅ ለሌሎች ጓዶች የሚጨነቅና ቅድሚያ የሚሰጥ ነበር፡፡ ምግብ በምንመገብበት ጊዜ አንድ ሰው ምግቡን ቀድሞ ከጨረሰና ቅር ብሎት ከተመለከተ፣ ፀጋዬ የራሱን ድርሻ ሲሰጥ ማየት የተለመደ ነበር፡፡ በበርሃ ውስጥ ከሚፈትኑን ችግሮች አንዱ የነበረው የልብስና የፀጉር ቅማል ነበር፡፡ መቸም ማከክን ተላምደነው እጃችን ስራ ፈቶ አይቆይም፡፡ ችግሩ ጠንከር ሲልም ለማስታገስ እርስ በርስ መቀማመል የተለመደ ሲሆን፣ ፀጋዬን ግን የሚያህለው አልነበረም፡፡ ጊዜ ኑሮት አንድ ሰው ሲያክ ካየ ዝም አይልም፣ ጠጋ ብሎ ይለቅምለትና እናት የልጇን ራስ እንደምትደባብስ ሁሉ እሱም በደስታ ይደባብሳል፡፡ በተለይ ሰፋ ያለ ጊዜ ካለው፣ እሱ እንዲቀምለን ተራ የምንገባበት ወቅት እንደ ነበረ ትዝ ይለኛል፡፡ እሱ ግን አይሰለችም፡፡ የእርካታ ስሜት ነበር የሚታይበት፡፡" (የአሲምባ ፍቅር፣ ገፅ 106)

በነገራችን ላይ እነዚህ ተዳፍነው የነበሩ ታሪኮች መውጣታቸው፣ አንድም የዚያ ዘመን ትውልድ ያለፈበትን የህይወት እውነት ለመረዳት፣ ሁለትም ለባለ ታሪኮች ቤተሰቦችም ሆነ ለታሪክ፣ እንደ ማስታወሻነትም እንደ ታሪክ ሰነድነትም ያገለግላል፡፡ ለምሳሌ ከዓመታት በኋላ የወንድሙን ታሪክ ከዚህ መፅኃፍ ያነበበው፣ የፀጋዬ ገብረ መድህን ወይም የፀጋዬ ደብተራው ወንድም ገብርኤል ገብረ መድህን፣ በሶስተኛው እትም ላይ የተሰማውን ስሜት እንዲህ ገልፆታል፡፡

"ስለ ፀጋዬ ብዙም የማውቀው ነገር አልነበረም፡፡ በቤተሰባችን ውስጥ ፀጋዬ ታይቶ እንደጠፋ ህልም ነው፡፡ ሳንጨብጠው የቀረብን ቅዠት፣ አሁን ግን የአሲምባ ፍቅር በሚለው መፅሃፍ እሱ ጋር ቅርብ የነበረ ሰው፣ ብዙም ሳላውቀው ስለተለየኝ ወንድሜ ታሪክ ሲተርክ ሳነብ፣ በጣም ነው ስሜቴን የነካው፡፡ በተለይ ቅማሉን ሲቀምሉለትና እሱም ሲቀምልላቸው የነበሩ ጓደኞቹ፣ ከእሱ ጋር ጫካ ለጫካ ሲንከራተቱ የነበሩ የቅርብ ሰዎች፣ ታሪካቸውን ሲፅፉ ሳይ ፀጋዬን ቅርቤ ድረስ ያመጡልኝ ያህል ነው የተደሰትኩት፡፡"

ሌላው አብነት የሚሆነን ኤርትራ እያለ በተማረው መጠነኛ የህክምና ሙያ፣ ታጋይ ጓዶቹን የሚያሰለጥነው ጌራ ነው፡፡ ለአሰልጣኞቻቸው ክንዳቸውን ዘርግተው መርፌ እየተወጉ የሚሰለጥኑ ታጋዮች እንዳይጎዱ፣ ብዙ ጊዜ ፀጋዬ ደብተራው ነበር መለማመጃ ሆኖ የሚቀርበው፡፡

"...ጌራ የህክምና ሙያ ስልጠና የወሰደው ከአራት ጓዶቹ ጋር ጠፍተው ከኢትዮጵያ ለመውጣት ሲሞክሩ ሶማሊያ ውስጥ ታስረው ከተፈቱ በኋላ ነበር፡፡ ከእስር ሲፈቱ አብረው

ከነበሩ የኤርትራ ተወላጅ ተማሪዎች ጋር ወደ ኤርትራ ከገቡ በኋላ በኢ.ፒ ፒ ኤፍ (ሻዕቢያ) ዶክተሮች አማክኝነት ሰለጠኑ፡፡ ጌራ ኅበዝና ታታሪ አሰልጣኝ ከመሆኑም ሌላ ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ የህክምና ዕርዳታ የሚያደርግልን እሱ ስለ ነበር በቅፅል ስም ዶክተር እያልን እንጠራው ነበር፡፡" (የአሲምባ ፍቅር፣ ገፅ 58፡፡)

እውነተኛ ታሪኮችን የያዘው ይህ መፅሃፍ የእነዚያ ታጋዮች ታሪክና ኑሮ እንዴት እንደ ነበር ማንበብ አንድም ያማል፣ ሁለትም ያ ትውልድ የከፈለውን መራር የህይወት እውነት፣ ፍንትው አድርጎ ያሳያል ብዬ አምናለሁ፡፡

## *የካህሳይ ኩርባዎች ሶስት- ጉራ ወርቂና ይመር ንጉሴ*

በአሲምባ የነበረው የኢህአፓ የሰራዊት ክንፍ ወይም ኢህአሰ፣ የተለያዩ ወታደራዊ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ የትጥቅ ትግል ጀምሮ ነበር፡፡ አንዱ ደግሞ በ1968 ዓ.ም በወልዲያ ያደረገው ኦፕሬሽን ነበር፡፡ በዚህም አንድ ቡድን ወደ ወልድያ ከተማ ተንቀሳቅሶ፣ የወልድያን ባንክ ለመዝረፍ እቅድ ተነድፏል፡፡ እቅዱን ለማስፈፀም ከተሰለፉት ታጋዮች መካከል ደግሞ የያኔው ታጋይ አማኑኤል፣ የአሁኑ "የአሲምባ ፍቅር" ደራሲ ካህሳይ አብሮ ነበር፡፡ ነገር ግን የታሰበው የወልዲያ እቅድ በመክሸፉ ወደ አሲምባ መመለስ ግድ ይላቸው ነበር፡፡ እናም በሮቢት አድርገው ለመጓዝ ተንቀሳቀሱ፡፡ ውድዬ፣ ጉራ ወርቂ በተባለች የወሎ አንድ የገጠር መንደር ውስጥ፣ የኢህአሰ አባላት ያጋጠማቸውን ሁኔታ ደራሲው በመፅሃፍ ውስጥ ገጠመኙን አስፍሯል፡፡

"ሰኔ 26 1968 ውድዬ ስንደርስ እኩለ ቀን ሆኗል፡፡ ከዚያ አረፍንና ህዝቡን አነጋግረን፣ አስተባበርንና የሚበላና የሚጠጣ ሰጡን፡፡ አንዳንድ ጓዶች እንደ ደከሙ ነበሩና እረፍት ያስፈልግ ነበር፡፡" ይላል፡፡ (የአሲምባ ፍቅር፣ ገፅ 120)

የደከማቸው ታጋዮች እረፍት አደረጉ፡፡ ደራሲውና ፍሱህ ገብራይ የተባለው ታጋይ፣ ተጨማሪ ምግብ ፍለጋ ወደ መንደሩ አቀኑ፡፡ መንገዳቸው ላይ እንደ አካባቢው ግልድም አገልድሞ፣ ከላይ ኮት የለበሰ ገበሬ ያገኛሉ፡፡ አለባበሱና አነጋገሩ ከተማ ቀመስ ነበር፡፡ ጥሩ ጠመንጃ ይዟል፡፡ ምግብ ሲያሰባስቡም ያግዛቸዋል፡፡

"...ከዚያ በኋላ ገበሬው፣ ለያዘው መሳሪያ ጥይት እንድሰጠው ጠየቀኝ፣ ልሰጠው ብፈልግም የእርሱ ጠመንጃ አልቀበል አለ፡፡ እሱ ጥይት ልሰጠው ስለሞከርኩለት ደስ ብሎታል፡፡ እኔ ደግሞ እገዛ ስላደረገልን ብሰጠው እደሰት ነበር፡፡ መጨረሻ... 'ጋሼ! በቃ

ተወው፤ በሙከራህ ብቻ ሚሊዮን ጥይት እንደሰጠሽኝ ነው የምቆጥረው፤ ሌላ ጊዜ ስትመለስ ግን የኔ አይነት መሳሪያ የሚበላውን ጥይት ይዘህልኝ እንድትመጣ?' አለኝና በዚሁ ተለያየን፡፡" (የአሲምባ ፍቅር፤ ገፅ 120)

ከዚህ በኋላ አመሻሽ ላይ ከውድዬ ተነስተው ወደ ጉራ ወርቄ ያመራሉ፡፡ ሌሊቱን በጉዞ አሳልፈው ፤ንጋት ላይ ሜዳውን ጨርሰው፤ ተራራውን መውጣት ይጀምራሉ፡፡ ይሁን እንጅ ጉዟቸው ሰላማዊ አልነበረም፡፡ የገበሬ ሚኒሻ ታጣቂዎች እየተከተሏቸው ነበር፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ተኩስ ይከፈትባቸዋል፡፡ አንድ ታጋይም ይማረካል፡፡ በዚህ ሁኔታ ሃይላቸው ለሁለት ይከፈላል፡፡ ከኋላ ደግሞ ተኩሱ ጠነከረ፤ ወደ ኋላ እየተኮሱ ወደ ፊት ይሄዳሉ፡፡ በታጣቂዎች ከመከበብ ግን አላመለጡም ነበር፡፡ ደራሲው ያችን ቅፅበት እንዲህ ገልጿታል፡፡

"...መከበባችንን ካወቅን ከትንሽ ጊዜ በኋላ፤ ብርሃነ እያሱና ተስፋዬ ደሳለኝ ተኩስ አቁመን ከህዝቡ ጋር እንድንነጋገር ሀሳብ አቀረቡ፡፡ በዚህ ጊዜ ከእኛ ውስጥ ጥይት ያለቀባቸውና ወደ ፊት ያስቀደምናቸው ጓዶች ቁጥር እየጨመረ መጥቷል፡፡ በመታኮስ ላይ የነበርነውና ወደ ኋላ የቀረነው አስራ ሁለት ብንሆን ነው፡፡" (የአሲምባ ፍቅር፤ ገፅ 123)

ብርሃነና ተስፋዬ የተባሉ ታጋዮች "እኛ እናንተን የምንወጋ ሰዎች አይደለንም፤ የእናንተ ወገኖች ነን፤ ተጋዳዮች ነን!" እያሉ ለማግባባት ይሞክራሉ፡፡ ነገር ግን ሚኒሻዎቹ ተኩሱን ቆም አድርገው፤ እየተሹለከለኩ በጣም መጠጋት ጀመሩ፡፡

"...እኔ ዘሚካኤልና ጁሊያኖ መካከል ሆኜ እተኩሳለሁ፡፡ ጁሊያኖ ብዙ አልቆየም፤ አንዱ ገበሬ፣ ከበስተጀርባው መጥቶ ጭንቅላቱን በመጥረቢያ ፈለጠው፡፡ ደሙ እንደ ሀይለኛ የምንጭ ውሃ እየፈለቀ፤ ከአናቱ በላይ እየተረጨ፤ መፈነጣጠቅ ጀመረ፡፡ ከዚያ ደሙ እየተንዠቀዠቀ ወርዶ፤ በደሙ ሲታጠብና ተሽከርክሮ ሲወድቅ አየሁት፡፡ አጠገቡ የነበረው መገርሳ፣ ጥይት አልቆበት ባዶ ጠመንጃ ነበር የያዘው፡፡" (የአሲምባ ፍቅር፤ ገፅ 123)

መገርሳ በእልህ ጁሊያኖን የፈነከተውን ሰው ግብ ግብ ይዞ፤ በጣም የተጎዳውን ጓደኛውን ይጣራል፡፡ "ጁሊያኖ!... ጁሊያኖ!" እያለ ይጮሃል፡፡

“…ዞር ብዬ ስመለከት ያ!… ሁላችን በጣም የምንወደው ጁሊያኖ መሆኑን ገና ያወቅሁ ይመስል እንባ በእንባ ሆንሁ፡፡ …ወዲያው ደግሞ… አሊጋዝን ከተፋላሚዎች አንዱ በጩቤ ወግቶ ጣለው…” (የአሲምባ ፍቅር፣ ገፅ 124)

በዚህ መልኩ ድብልቅልቅ ያለ ውጊያ ሆነ፡፡ ጥይት የጨረሱ ታጋዮች የጨበጣ ውጊያ ጀመሩ፡፡

“…ወደ ግራ ገልመጥ ገልመጥ በማለት ወደ ፊት ለማተኮር ወሰኘ፣ ጠመንጃዬን ደገንኩና ልተኩስ ስል፣ ከጀርባዬ የኮቴ ድምፅ የሰማሁ መሰለኝ፡፡ ለማረጋገጥ ዞር አልኩ፣ አንድ ግዙፍ ሰው ከእሾሃማው ጫካ ውስጥ ዘሎ ወደ እኔ ሲመጣ ተመለከትሁ፡፡” (የአሲምባ ፍቅር፣ ገፅ 124)

ከጀርባው የመጣው ሰው ሽምገል ያለ ግዙፍ አርሶ አደር ነበር፡፡ ታጋዩ ወላወለ፡፡

“…ጠመንጃዬን ልተኩስ ከደገንሁበት በኋላ አመነታሁና ተውኩት፡፡ ዙሪያዬ የነበረው ድርጊት ምንም ተስፋ እንደሌለው ያሳያል፡፡ ያነጣጠርኩበትን ገበሬ ያለ ምንም ጥቅም እንደምገለው በዚያ ሁኔታ ውስጥ ሆኘ ማሰቤን ሳስታውሰው ዛሬም ይገርመኛል፡፡ …እኔ በመተኮስና ባለ መተኮስ መካከል ሳመነታ ሰውዬው አጠገቤ ደርሶ ጭንቅላቴ ላይ ሰፈረብኝ፡፡ ተያይዘን ወደቅን፡፡ ራሴን ለመከላከል ምንም ፋታ አልነበረኝም፡፡” (የአሲምባ ፍቅር፣ ገፅ 124)

አስቡት?… እየተኮሱ ጓደኞቹን የሚጥሉትን… በመጥረቢያ የጓዶቹን ጭንቅላት የሚያፈርሱትን… በጦር አንጀታቸውን ሲርሷቸው… እያዩ… በዚያ የደም አበላ መካከል አንድም ሰብአዊነት፣ ሁለትም አስከፊውን ስርዐት ገርስሰው፣ ነፃነቱን ሊያስከብሩለት ያሰቡት ህዝብ፣ በተሳሳተ ፕሮፖጋንዳ ወይም በደርግ ጫና የጣጠቁ ሰዎች ፊት ለፊት ሲመጡ… ጣታችሁ ከጠመንጃው ምላጭ ላይ አርፎ፣ ተኩሳችሁ መምታት ስትችሉ፣ የወጣችሁለትን ህዝባዊ አላማ አስባችሁ በምርኮ ስትወድቁ…

“ጥይት አልጨረስክም፣ እየተታኮስክ እንደነበርም አይቻለሁ፣ ታዲያ ለምን አልተኮስክብኝም?” ብሎ ጠየቀኝ፡፡

“እንኳንም አልገደልሁህ!” አልሁት ድንገት፡፡ የተናገርሁትን ሲሰማ ገርሞት

“ምን ማለትህ ነው?” አለኝ፡፡ በያዘው ገመድ በተኛሁበት እጆቸን ለማሰር ተዘጋጀ፡፡ (የአሲምባ ፍቅር፣ ገፅ 124-125)

በዚህች ቅፅበት ውድዬ ምግብ ፍለጋ ሲሄዱ ያገኛቸው ገበሬ እየሮጠ ይመጣል፡፡ በምርኮ የተያዘው ሰው ለጠመንጃው ጥይት ሊሰጠው ፈልጎ፣ ሲሞክርለት የነበው ታጋይ ነው፡፡ እናም እንደ ውለታ ቆጥሮት እንዳትገሉት ማለት ጀመረ፡፡ ምረኮኛው ታጋይ ግን በግዙፉ አርሶ አደር እጅ ገብቷል፡፡ ታጋዩ ግን እውነቱን የኑዛዜ ያህል ይናገር ነበር፡፡

“አንተ ምናልባት ሚስትና ልጅ እንዲሁም ሌሎችም የምታሳድራቸው ብዙ ሰዎች ሊኖሩህ ይችላሉ፡፡ እኔ ግን የማሳድረው ቤተሰብ የለኝም፡፡ ብትገለኝም እንኳን አንድ ብቻዬን ነኝና ግድ የለኝም፡፡ አንተን ብገድልህ ልጅህና ሚስትህ ሊቸገሩ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ እኔ አንተን ከምገድልህ፣ አንተ እኔን ብትገድለኝ ይሻላል፡፡ አልኩትና ከወደቅሁበት ተነሳሁ፡፡ ማሰሩን ተወና አጠገቤ ቆሞ ይጠብቀኝ ጀመር፡፡” (የአሲምባ ፍቅር፣ ገፅ 125)

ይች ቅፅበት የታጋይ አማኑኤልን እጣ ፈንታ ቀየረች፡፡ ከዚያ ከጉራ ወርቄ ግዙፍ አርሶ አደር፣ ከይመር ንጉሴ ጋር በዚህ መልኩ ተዋወቁ፡፡ እናም ይመር ንጉሴ እንኳን ሊገድለው ይቅርና የደርግ ሰዎች እንዳይለዩት፣ እንደ አካባቢው ሰው ግልድም አስለበሰው፡፡ ገንዘብ ሰጠው፣ ሮቢት ድረስ ሸኝቶ፣ በአውቶብስ አሳፍሮ ወደ አሲምባ አሻገረው፡፡ ለዚያ ነው ደራሲና ጋዜጠኛ ነብይ መኮንን ይመር ንጉሴንና አማኑኤልን ህይወት ተቀባበሉ ያለው፡፡

ታጋይ አማኑኤል ከሞት ተርፎ፣ የህይዎት ኩርባዎቹን ሲዞር፣ የዚያን ዘመን አውነትና ያን የጉራ ወርቄውን ገበሬ ይመር ንጉሴን አልረሳውም ነበር፡፡ ከ30 አመታት በኋላ፣ ስደት ከሄደበት ሀገረ አሜሪካ ሲመለስ፣ መጀመሪያ ያቀናው ወደ ጉራ ወርቄ ነበር፡፡

“...ከአስፋልቱ በስተ ግራ በኩል የሚያመራ መንገድ ይዘን ስንሄድ፣ ወደ ገበያ የሚሄዱ አዛውንቶች አገኘንና መኪናችንን አቆምን፡፡ በዕድሜያቸው የገፉ የሀገር ሽማግሌ መሳይ ስለ ነበሩ፣ ሊያውቁ እንደሚችሉ ገምተናል፡፡ ይቅርታ ጠይቀን አስቆምናቸውና ‘እዚህ አካባቢ የሚኖር ሰው ብንጠይቃችሁ ታውቃላችሁ?’ አልናቸው፡፡ አንደኛው ሰውዬ ‘መሀመድ እባላለሁ፣ እዚሁ አካባቢ ነው ሀገሬ፣ እዚህ ወጣ ብሎ ይሄንን ጋራ ተሻግራችሁ ነው፡፡ ማንን ፈልጋችሁ ነው? ስሙን ታውቂታላችሁ?’ አሉን፡፡”

“ይመር ንጉሴ የሚባል ሰው” አልኳቸው፡፡

“ይመር ንጉሴ? ወይ ወንድሜን!” ብለው ጭንቅላታቸውን ይዘው ማልቀስ ጀመሩ፡፡

ልቤ ስንጥቅ አለ፡፡ መጠየቅ አስፈላጊ አልነበረም፤ አውቄዋለሁ፡፡ እውነቱን መቀበል ግን አልፈለግሁም፡፡ ለመናገር መዘጋጀቴን ሳላውቀው ከአፌ “ምነው?” የሚል ቃል ሲወጣ በጆሮዎቸ ተሰማኝ፡፡

“ይመር ንጉሴ እኮ ሞቷል!” አሉ፡፡ (የአሲምባ ፍቅር፤ ገፅ 20-22)

ደራሲው ይመር ንጉሴን በህይወት አላገኘውም፡፡ ነገር ግን ተስፋ ቆርጦ አልተመለሰም፡፡ በህይወት ያሉ ልጆቹንና ባለቤቱን ማፈላለግ ቀጠለ፡፡ የይመር ንጉሴን ባለቤት አገኛቸው፡፡ ነገር ግን ሊያውቁት አልቻሉም ነበር፡፡ የነበረውን ታሪክ ሲነግራቸው ግን ምርር ብለው አለቀሱ፡፡

“…በእርግጥ ይመር ንጉሴ እድሜው ሄዶ ነበር፡፡ እና ለባለቤቱ ታሪኬን ስነግራት አዘነች፡፡ አየህ?... ከመሞቱ በፊት ስለ እኔ ያስብ ነበር፡፡ ምክንያቱም ወቅቱ አስቸጋሪ ስለ ነበር፤ አሲምባ ደርሸ ከጓዶቸ ጋር ሳልገናኝ፤ መንገድ ላይ የሞትሁ ይመስለው ነበር መሰለኝ፡፡ ባለቤቱም የነገረችኝ ይህን ነበር፡፡ ‘…አይይ… ያልጅ እንዴት ሁኖ ይሆን?... እንዲያው የደርግ ታጣቂዎች አግኝተው ገለውት ይሆን?... ወይስ በሰላም ገብቶ ይሆን?... እንዲያው ሰላም ባይሆን እንጅ… ደህና ቢሆን ኑሮማ መልክት ሳይልክብኝ አይቀርም ነበር… እያለ  ሁል ጊዜ ይጨነቅ ነበር፡፡’ ብለው ሲነግሩኝ በጣም አዘንሁ፡፡” ነበር ያለኝ፤ ታሪኩን ሲነግረኝ፡፡

ያም ሆኖ ግን ነፍስ የተቀባበለውን ገበሬ አግኝቶ እንዳሰበው ባያመሰግነውም፤ ውለታውን ለቤተሰቦቹ መልሷል፤ ታሪኩን ደግሞ ለአንባቢ አቅርቦታል፡፡ በነገራችን ላይ ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ሀገር ቤት ሲመጣ ከደራሲው ጋር ተገናኝቸ ነበር፡፡ የሚገርመው ልክ እንደ ቤተሰቦቹ ጉራ ወርቄ ሄዶ የይመር ንጉሴን ቤተሰቦች ጠይቋቸው ነበር፡፡ ምክንያቱም ደራሲው በህይወት ኑሮ ታሪኩን ይነግረን ዘንድ፤ ያ ደግ የወሎ ገበሬ ይመር ንጉሴ ባለ ውለታው ነበር፡፡ ያ ትውልድ እንደዚህ ነበር… ሳምንት ይቀጥላል…

# የካህሳይ ኩርባዎች

## ክፍል ሶስት

*በሽጋው ሙሉማር*

ጤና ይስጥልኝ አንባቢዎች? ባለፉት ሁለት ተከታታይ እትሞች “የአሲምባ ፍቅር” የተሰኘውን መፅሃፍ በወፍ በረር ማስቃኘቴ ይታወሳል፡፡ ደራሲው በአሲምባ በነበረው የኢትዮጵያ ህዝባዊ አብዮታዊ ሰራዊት ወይም ኢህአሰ በተባለው የኢህአፓ ወታደራዊ ክንፍ ውስጥ የነበረ ታጋይ ሲሆን፣ በትግል ህይወቱ ያሳለፈውን ውጣ ውረድ፣ አንድም ከመፅሃፉና ከሌሎች ተዛማች ታሪኮች ጋር እያነፃፀርሁ፣ ሁለትም ከደራሲው ጋር በነበረኝን ቆይታ የሰማሁትን ታሪክ መሰረት አድርጌ፣ ዳሰሳ አድርጌ ነበር፡፡ በዛሬው የመጨረሻ ክፍል ፁሁፌ ደግሞ፣ ደራሲው በአሲምባ በነበረበት ጊዜ ያጋጠመውን የትግልና የፍቅር ህይወት እዳስሳለሁ፡፡ መልካም ንባብ…

በትግል ውስጥ የዓላማ ፅናት አለ፡፡ በትግል ውስጥ ፍቅር አለ፡፡ ፍቅራቸው ግን የጓድነትና በህዝባዊ ዓላማ መተሳሰር እንጅ፣ በተቃራኒ ፆታ መጣመር አልነበረም፡፡ ምክንያቱም በድርጅቱ ውስጥ የተቃራኒ ፆታ ፍቅር ክልክል ነበር፡፡ ከዓላማ ያዘናጋል የሚል እምነት ስለ ነበራቸው፡፡

ነገር ግን ፍቅር ሰብዓዊ ነው፡፡ ይህ ሰብዓዊነት ከዓላማችን ያናጥበናል ብለው ያሰቡት የዚያ ትውልድ ወጣቶች፣ አስከሬ የሚሉትን ስርዐት ለመገርሰስ፣ የዓላማ ፅናትን እንጅ ሰብዓዊነትን ዘንግተውታል፡፡ የሚገርመው ደግሞ  ሴትና ወንድ አንድ ላይ ተኝተው (በትጥቅ ትግሉ ወቅት በተለይ የኢህአፓ ታጋዮች ሁለት ሁለት ሆነው ነበር የሚተኙት፡፡) እንኳን ያነገቡትን ህዝባዊ ዓላማ እንጅ፣ ሰዋዊ የሆነውን የተቃራኒ ፆታ ስጋዊ ግንኙነት፣ ትኩረት አይሰጡትም ነበር፡፡

አበው ሴትና ወንድ እሳትና ጭድ ነው ቢሉም ቅሉ፣ በትጥቅ ትግሉ ወቅት የነበሩ ታጋዮች ግን እንደዚያ አልነበሩም፡፡  በአንድ ወቅት የኢህዴን ታጋይ ከነበረ ወዳጀ ጋር በዚህ ጉዳይ ላይ ስንጨዋወት ገጠመኙን ነግሮኝ ነበር፡፡

“አላማችን ትግል ነው፡፡ በዚያ ላይ በድርጅቱ ውስጥ የፍቅር ግንኙነት ክልክል ነበር፡፡ እኔ ትዝ የሚለኝ ብዙ ጊዜ ተልዕኮ ተሰጥቶን ስንንቀሳቀስ፣ አንዲት ታጋይ አብራኝ ትሄድ

ነበር፡፡ ያው ትግል ነውና ብዙ ጊዜ አብረን ነበር የምንተኛው፡፡ ዛሬም ድረስ ሳስበው የሚገርመኝ ግን፤ አብራኝ እየተኛች ምንም አይነት የተለየ ስሜት አልነበረኝም፡፡”

እርግጥ ነው የዚያ ትውልድ አባላት የተነሱለትን ህዝባዊ አደራ ዳር ለማድረስ ብዙ መስዋዕትነት ከፍለዋል፡፡ ራሳቸውን ለህዝብ እውነት አሳድረዋል፡፡ በአጠቃላይ የጓድነትና የትግል ፍቅር የበረታበት ነበር፡፡ ይህ ማለት ግን ታጋዩ ጭራሽ የፍቅር ፍላጎት አልነበረውም ማለት አይደለም፡፡ ብዙዎቹ ታጋዮች በዐይን ፍቅር ሲከንፉ እንደ ነበር፤ በደራሲ ካህሳይ “የአሲምባ ፍቅር” ውስጥ ተጠቅሷል፡፡ መፅሃፉ ከታተመ በኋላ ታጋይ የነበሩ ሰዎች የነበራቸውን ገጠመኝ ለደራሲው እንደነገሩት አጫውቶኛል፡፡

“…በአሲምባ የነበሩ ጓዶች ነበሩ፡፡ አሁን ውጭ ሀገር ነው የሚኖሩት፡፡ እነዚህ ታጋዮች በትግሉ ወቅት በዐይን ፍቅር ወድቀው ነበር፡፡ በኋላ ከአቅማቸው በላይ ይሆናል፡፡ እናም በድብቅ ፍቅር ይጀምራሉ፡፡ ያን ጊዜ በጣም ክልክል ስለሆነ አዩኝ አላዩኝ ብለህ ነው፡፡ ታዲያ እነዚህ በፍቅር የወደቁ ታጋዮች ፍቅራቸውን አምቀው ኖሩ፡፡ ድርጅቱ ፈርሶ ታጋዩ ከተበታተነ በኋላ፤ ወደ ውጭ ሀገር ይሄዳሉ፡፡ እዚያ ፍቅራቸውን በነፃነት ተወጡ፡፡ አሁንም ተጋብተው ነው የሚኖሩት፡፡”

### *የካህሳይ ኩርባዎች አራት- አማኑኤልና ድላይ*

በትጥቅ ትግሉ ወቅት ለሴት ታጋዮች ፈታኝ የነበረው የወር አበባ ነው፡፡ ቅልጥ ባለ ውጊያ ውስጥ ይመጣል፡፡ አማራጭ የለምና ጭናቸው እየተላጠ፤ ደም እየፈሰሳቸው ይዋጋሉ፡፡ ልብሳቸው በደም ይላቁጣል፡፡ እዚህ ላይ የአንዲትን የኢህዴን ታጋይ ገጠመኝ ልጥቀስ…

“…የወር አበባዬ መምጣቱን መናገር አልፈለግሁም፡፡ ምክንያቱም የምንሄደው ወደ ጦርነት ነው፡፡ ስለዚህ ሊያስቀሩኝ ይችላሉ፡፡ ዝም ብዬ ተጓዝሁ፡፡ ወዲያው ሀይለኛ ጦርነት ተጀመረ፡፡ በአንድ በኩል ከደርግ ጋር እዋጋለሁ፡፡ በሌላ በኩል ከሴትነት ተፈጥሮዬ ጋር እታገላለሁ፡፡ ደም ሲፈሰኝ ይታወቀኛል፡፡ ግን ውጊያው ከባድ ነውና እያመመኝም ቢሆን መዋጋቱን ቀጠልሁ፡፡ ከሰዓታት በኋላ በድል አጠናቀን፤ መጨፈር ስንጀምር ህመሙ በረታብኝ፡፡ ጓዶቸ ሁኔታዬን ሲያዩ ደነገጡ፡፡የተመታሁ ነበር የመሰላቸው፡፡ ለካን ልብሴ በደም ተጨማልቆ ነበር፡፡ እውነቱን ስነግራቸው ተቆጡኝ፤ ተጣጠብሁ፡፡ አየህ ሴትነት መንታ ትግል ነበር፡፡” ትላለች፡፡

ደራሲ ካህሳይ ወደ ትግል ወጥቶ፣ የኢህአሰን ሰራዊት የተቀላቀለው በአፍላ ዕድሜው ነበር፡፡ ለትግል ብቻ ሳይሆን ለተቃራኒ ፆታዊ ፍቅርም እንግዳ ነበር፡፡ ነገር ግን በአሲምባ በነበረበት ወቅት፣ በአንዲት ምሽት የህይወት መስመሩ ኩርባ ወደ ተለየ አቅጣጫ ይታጠፋል፡፡ የካህሳይና የድላይ የፍቅር ኩርባዎች የሚጀምረው ከአሲምባ ነው፡፡

ድላይ በአሲምባ ውስጥ በነበረው የኢህአሰ ሰራዊት ውስጥ ስመ ጥር ታጋይና የሀይል ምክትል አመራር ነበረች፡፡ እንደ ብዙ ሴት ታጋዮች ሁሉ የድላይ ትግል ከስርዐቱ ጋር ብቻ ሳይሆን፣ ተፈጥሮ ለሴቶች ብቻ ከሰጠቻቸው ፀጋ፣ ከወር አበባቸው ጋርም ነበር፡፡

ሞዴስ ብሎ ነገር በትጥቅ ትግሉ ወቅት አይታሰብም፡፡ ለእነሱ ሞዴሳቸው ቀን ቀን አንገታቸው ላይ የሚጠመጥሚት፣ ማታ እንደ ብርድ ልብስ የሚለብሷት፣ የወር አበባቸው ሲመጣ አጣጥፈው እንደ ሞዴስ የሚጠቀሙባት፣ መስዋዕት ሲሆኑ የሚገነዙባት ክሹፋቸው ብቻ ነበረች፡፡ ምናልባት ወደ ከተማ ከተጠጉ ከተማ ውስጥ ከሚኖሩ አባሎች ሊወስዱ ይችላሉ፡፡ እሱም ቢሆን ከተገኘ ነው፡፡

ከእቻ ልጃገረዶች ጋር በወጉ ሳይጫወት፣ በለጋ እድሜው ወደ ትግል የገባው የያኔው ታጋይ አማኑኤል፣ የአሁኑ ደራሲ ካህሳይ፣ በኢህአሰ ውስጥ እያለ የህይወት ኩርባውን የለወጠውና ከድላይ ጋር በፍቅር ያጣመረው አጋጣሚም ከዚህ ጋር የተያያዘ ነበር፡፡

አንድ ቀን የአብዩ ከአንድ ጓድ ጋር ወደ አማኑኤል ይሄዳል፡፡ ድላይ ልብሷ ስለ ተበላሸ ማጠብ ነበረባት፡፡ ምክንያቱም በትግሉ ወቅት ቅያር ልብስ አልነበረም፡፡ ለዚህ ነበር የአብዩ አማኑኤልን ሱሪህን ለድላይ ስጣት ያለው፡፡

“ምንድን ነው የምሰጣት? እየቀለዳችሁ ነው?” አልኩ ሳቃቸው እየተጋባብኝ፡፡

“የለም ለመቀለድ አይደለም የመጣነው፣ ድላይ ልብሷን ለማጠብ ወደ ወንዝ ስለ ምትሄድ፣ የአንተን ሱሪ ለጊዜው እንድትሰጣት ልንጠይቅህ ነው፡፡” አሉኝ፡፡

“እኔስ ምን ልለብስ?” አልኳቸው የሚሉት ግራ ገብቶኝ፡፡

“እንደ ልማድህ ነጠላውን ፍታውና አገልድም፡፡” አለኝ የአቢዩ አሁንም እየሳቀ፡፡ (እንደ ልማድህ ማለቱ ከወሎ ስመለስ በአገልድም ወደ አሲምባ የገባሁትን አስታውሶ ነው፡፡) (የአሲምባ ፍቅር፣ ገፅ 247)

አማኑኤልም ሆነ ድላይ ከጓድነት የዘለለ የፍቅር እሳቤ አልነበራቸውም፡፡ ተፈጥሮ በራሱ መንገድ አገናኛቸው እንጅ፡፡ እናም የሰጣትን ሱሪ ስትመልስለት ታመሰግነዋለች፡፡ ግንኙነታቸው ግን በዚህ አላበቃም ነበር፡፡ ልብሷን ብታጥብም ደም እየፈሰሳት ስለ ነበር፣ ወገቧን በጣም አመማት፡፡ ትጥቋን አውርዳ ሽጉጥ ብቻ ታጥቃለች፡፡ ይህም ሆኖ የሚፈሳትን ደም ለማቆም ሞዴስ ያስፈልጋታል፡፡ ያላት አማራጭ ከአሲምባ ወደ ነበለት ከተማ ሄዳ፣ ከመምህራኖች ሞዴስ መለመን ነበር፡፡ እናም በአማኑኤል አጃቢነት ወደ ነበለት ጉዞ ይጀምራሉ፡፡

ድላይ የምታመጣው እቃ ስላለ አብረሃት ሂድ የተባለው አማኑኤል፣ በጉዟቸው ድላይ በተደጋጋሚ መፀዳዳት እንደምትፈልግ ስትነግረው፣ የገባው ነገር አልነበረም፡፡ ያ ስለ ሴት ልጅ ተፈጥሮ ከቀለም ትምህርት ውጭ ብዙም ግንዛቤ ያልነበረው ብላቴና፣ ለምን ወደ ነበለት እንደሚሄዱ ይጠይቃታል፡፡ ዘወርወር አድርጋ ብትነግረውም አልገባውምና ደጋግሞ ይጠይቃታል፡፡

እንዳልገባኝ ተረዳችና “የምናመጣው ዕቃ ሞዴስ ይባላል፡፡” አለችኝ፡፡

“ሞዴስ ምንድን ነው?”

“ሞዴስ ሴቶች ብቻ የሚጠቀሙበት የሴት ዕቃ ነው፡፡” አለችና ለአፍታ ያህል ስታስብ ቆየች፡፡ “ወንዶች እኮ እንደዚህ አይነት ነገር ስለማታውቁ ታድላችኋል፡፡” በድምጿ ውስጥ ሀዘን ተሰማኝ፡፡ ህመሟ ቀላል እንዳልሆነ ተረዳሁ፡፡ ግን ምን እንዳመማት በትክክል አልተረዳሁም….

“ታዲያ ሞዴስ ያሽልሻል ማለት ነው?” አልኳት፡፡

“አያሽለኝም፣ ግን ልብሴን ከመበላሸት ይጠብቅልኛል፣ ማለት ይከላከልልኛል፡፡ በየቀኑ ልብሴን ለማጠብ እንደማልችል አንተም ታውቃለህ፡፡” ብላ ስትገልፅልኝ፣ የእኔን ሱሪ ለምን ተውሳ እንደዋለች ብልጭታ ቢጤ ታየኝ፡፡ (የአሲምባ ፍቅር፣ ገፅ 250)

ከደራሲው ጋር በአካል ተገናኝተን እያለ በመፅሃፉ ውስጥ ያነበብሁትን ይህን ታሪክ አንስቼለት ነበር፡፡ ከሰላሳ ዓመታት በኋላ ትዝታውን ሲያጫውተኝ እየሳቀ ነበር፡፡

“እውነቱን ልንገርህ?... ሴት ልጅ የወር አበባ ስታይ፣ እንደሚያማት ለመጀመሪያ ጊዜ ያየሁት ያን ጊዜ ነበር፡፡ ሞዴስ ምን እንደሆነ እንኳን አላውቅም ነበር፡፡ ድላይ ስትነግረኝ ሁሉ አልገባኝም ነበር፡፡” ይላል፡፡ (የአሲምባ ፍቅር፣ ገፅ 250)

ነበለት ሲደርሱ መምህራኖች ደመወዝ ለመቀበል ወደ ከተማ ሄደዋል፡፡ ድላይ እድሏን አያማረረች፣ በዚያ ላይ ምሽቱ እየገፋ ወደ አሲምባ መመለስ ጀመሩ፡፡ ረጅሙን መንገድ ሲጨርሱ፣ የእምባ ሴኔትን ተራራ በድቅድቅ ጨለማ እየተዋጠ ነበር፡፡ ተራረውን እየቧጠጡ ይወጣሉ፡፡ ሰማይ መስኮቱን ከፍቶ በነጎድጓድ የታጀበ ዝናቡን ያወርደዋል፡፡ በዚያ ላይ ድላይ ቶሎ ቶሎ ትፀዳዳለች፡፡ በህመም እያቃሰተች፣ በጨለማው እየተደናበረች፣ አማኑኤልን ትከተላለች፡፡ እንዳይደረስ የለም ሰራዊቱ ካረፈበት አካባቢ ይደርሳሉ፡፡

ሁኔታቸውን ላያቸው በዝናብ የራሱ ሳይሆን ከውሃ የተሰሩ ይመስሉ ነበር፡፡ ይህን ያዩ ታጋዮች አንድ ቤት ውስጥ እሳት አንድደው፣ ልብሳቸውን ሳያወልቁ፣ ከእሳቱ ዳር ሆነው እንዲያዳርቁ ይደረጋል፡፡ እንደ ደንባቸው ክሹካቸውን አንጠፈው፣ ድላይ ወደ እሳቱ፣ አማኑኤል ደግሞ በጀርባዋ ይተኛል፡፡ ድላይ ሰውነቷ ይንቀጠቀጣል፡፡

እንኳን ሴት አቅፎ መተኛት ይቅርና ብዙም ከሴት ጎን ተቀምጦ የማያውቀው አማኑኤል፣ ሁኔታዋ ስላሳዘነው አቀፋት፡፡ ሙቀቱ ከልብሳቸው አልፎ ውስጣቸውን ማንደድ ጀመረ፡፡ ስሜታቸው ከድርጅቱ ህገ ደንብ በላይ ሰብዓዊነታቸውን ጠራው፡፡ ስሜታቸው ሸፈተ፡፡ መተቃቀፋቸውና እሳቱ የፈጠረባቸው ሙቀት ግን፣ የአማኑኤልን የህይወት ኩርባ ወደ ሌላ  አቅጣጫ ወሰደው፡፡

“...ድላይ ገልበጥ አለችና ፊቷን ወደ እኔ ዞረች፡፡ የሁለታችንም እሳት የሚተፋው ትንፋሽ ተቀላቀለና በላብ ተጠመቅን፡፡ አሁንም ወደ እኔ ጠጋ አለችና ሰውነቷ ከደረቴ ጋር ጥብቅ አለ፡፡ ከእኛ ቁጥጥር ውጭ በሆነ መግነጢሳዊ ስበት እየተጎተቱ ከንፈሮቻችን በጣም ተቀራረቡ፡፡ የከንፈሮቻችን ንክኪ ሙቀቱ፣ ጣዕሙ፣ ስሜቱ፣ ንዝረቱ ልዩ ነው፡፡ ፊፅሞ ሰላም የሰፈነበት ሌላ ውብ ዓለም ውስጥ ኸው ብለን ገባን፣ ያለንበትን ዘነጋነው...” (የአሲምባ ፍቅር፣ ገፅ 259)

የሁለቱ ብላቴና ታጋዮች ሁኔታ ቢታወቅ እስከ ሞት የሚያደርስ ቅጣት ይጠብቃቸዋል፡፡ እነሱ ግን በአፍላነታቸው ዘመን ለህዝብ ልዕልና ነበር በረሃ የወጡት፡፡ ነገር ግን በአንድ

አጋጣሚ በተቃራኒ ፆታዊ ፍቅር ወደቁ፡፡ ያም ሆኖ ግን ከመተቃቀፍ የዘለለ፣ ከዓላማ ፅናታቸው ሽብርክ እንዲሉ አላደረጋቸውም፡፡

አስቡት?... ከሴት ልጅ ጋር ተኝቶ የማያውቅ፣ የሴት ልጅን ውብ የገላ ጠረን ሳያጣጥም ወደ ትግል የገባው አማኑኤልና በተመሳሳይ የወንድ ልጅ ጠረን ምን እንደሆነ የማታውቀው፣ በዓላማ ፅናቷ፣ በጀግና ታጋይነቷና አመራርነቷ የምትታወቀው ድላይ እስከ ሞት የሚያደርሰው የተቃራኒ ፆታ ፍቅር በውስጣቸው ተፀነሰ፡፡ ዘፋኟ...

*እንዳይነጋ የለም ነጋብኝ ሌሊቱ፣*

***ጭንቅ ነው ጥብ ነው ካንተ መለየቱ...*** እንዳለችው እነዚያ ጥንድ ታጋዮች እንደተቃቀፉ ሰማይ ገለጠ፡፡ ያኔ ሁለቱም ለሰሩት ስህተት በውስጣቸው ይቅርታ ይጠይቃሉ፡፡ ምክንያቱም የድርጅቱን ህግ ስለጣሱ የዲሲፕሊን ቅጣት ይጠብቃቸው ነበር፡፡

"...ድላይ ማታ ከፍላጎትሽና ከዓላማችን ውጭ ሂጀ እንዳስቸገርሁሽ ተሰምቶኛል፣ በህመም ላይ ሆነሽ የወንድነት የተፈጥሮ ስሜቴን በጭፍን ተከትዬ ሳይታወቀኝ እንቅልፍ ነስቸሽ እንዳይሆን ስጋት አድሮብኝ ነበር፡፡" እያልኩኝ በማውቀው የተሰባበረ አማርኛዬ ነገርኳት፡፡

ገና ንግግሬን ሳልጨርስ "ምንም ስጋት እንዲያድርብህ አያስፈልግም፣ ከጠዋት እስከ ማታ ስታስታምመኝና ለእኔ ስትል ያሁሉ ዝናብ በጀርባህ ላይ ሲወርድ ውለህ አምሽተሃል፡፡ እኔ በጣም ደክሞኝና መሄድ አቅቶኝ እጀን ይዘህ ስትጎትተኝ ዋልህ፣ እንደገና ደግሞ ማታ እንዳይበርደኝ ለማድረግ ሌሊቱን በሙሉ ስትንከባከበኝ አደርክ፡፡ ይሄ ሁሉ ለእኔ በጣም ብዙ ነገር ነው፡፡ ስለዚህ ምንም እንዳታስብ፡፡ ብዙ ውለታ ጣልክብኝ እንጅ ምንም አላጠፋህም፡፡" ብላ በመሽኮርመም ፈገግ ስትልልኝ ታላቅ ደስታ ተሰማኝ፡፡ (የአሲምባ ፍቅር፣ ገፅ 261-262)

አማኑኤል በፍርሀት ውስጥ ገብቶ ሲያሳስበው የነበረውን ጉዳይ ቀለል አድርጋ አየችው፡፡ ምንም ስህተት እንዳልሰራ፣ እንዲያውም በወር አበባዋ ምክንያት ሳይጠየፍ ስላቀፋት፣ በጣም አመሰገነችው፡፡

በዚያች አንድ ሌሊት የተፈጠረው መቀራረብ የበለጠ መተሳሰብን ፈጠረላቸው፡፡ ነገር ግን ሁሉም ነገር በዓይንና በምልክት ብቻ እንጅ ገሃድ የወጣ አልነበረም፡፡ አንድ ዓላማ

ብቻ ሳይሆን፣ በውስጣቸው የተጫረው የፍቅር እሳት ውስጥ ውስጡን እየነደደ፣ የመሳሳብና የመተሳሰብን መንገድ ከፈተ፡፡

በአንድ ቀን አጋጣሚ የተጀመረው የድላይና የአማኑኤል የፍቅርና የትግል ጉዞ፣ ዳግም ብቻቸውን አገናኛቸው፡፡ በተፈጥሮ ደን ከተከበበው ከማይ ምሻም ተራራ የሚወርደው ፏፏቴ፣ ከተራራው ግርጌ የሚወርደው ወንዝና ለምለም የሆነው አካባቢ ለፍቅራቸው ድምቀት ታስቦ የተዘጋጀ የሚመስል ውብ ቦታ ነበር፡፡

"…እኔና ድላይም ገደሉን እየዘለልን፣ ጥሻውን እየጣስን፣ እየተያየንና በቅልጥፍና እየተራመድን፣ የግል ነፃነታችንን በማግኘታችን እየቦረቅን፣ በንግግራችን መሃል እየተሳሳቅን፣ እየተፍለቀለቅን ነበር የምንጓዘው፡፡ የፍቅርና የጓድ እንዲሁም የጓደኝነታችንን ልዩ ጥማት ለመወጣት ያስቻለንን እድል፣ በስሜት እንጅ በቃላት ለመግለፅ እንደማይቻል በደመ ነፍስ ታውቆን እየፈነጠዝን ወደ ፊት ገሰገስን፡፡" (የአሲምባ ፍቅር፣ ገፅ 286-287)

ፍቅርና ትግል በዚያ ዘመን እንዲህ ነበር፡፡ በነገራችን ላይ ደራሲው የማይ ምሻምን አካባቢ ለመግለፅ የተጠቀመበት ቋንቋ የሚገርም ነው፡፡ የቃላት አጠቃቀሙና የሀሳብ ፍሰቱ ምስል ከሳች ነው፡፡ ምንም እንኳን ደራሲው የተዋጣልኝ ነኝ ባይልም፡፡

"እኔ የስነ ፅሁፍ ፍቅሩ እንጅ ችሎታው የለኝም፡፡ ነገር ግን በወጣትነት እድሜዬ ተቀርፆ የቀረውን እውነት ለመፃፍ አልተቸገርሁም፡፡ ምክንያቱም ቦታዎችን በሚገባ አውቃቸዋለሁ፡፡ መፅሃፉን ያነበቡት ጓደኞቸ ሳይቀር በመፅሃፉ ስነ ፅሁፋዊ ውበት ተገርመው፣ ስትናገርና ስትፅፍ የተለያየህ ነህ ብለውኛል፡፡" ሲል ደራሲው በ2007 ዓ.ም መጨረሻ ነግሮኛል፡፡

"…የተቀመጥንበት ቦታ ደስ ይላል፡፡ ፀጥ ያለ ቦታ ነው፡፡ የሚሰማ ድምፅ ቢኖር የወፎች ጫጫታና ራቅ ብለው ቅጠላ ቅጠል እየበጠሱ የሚበሉ ፍየሎች ጩኸት ብቻ ነበር፡፡ ከፊታችን የአክሱም ሜዳ ተዘርግቷል፡፡ ወደ ላይ በኩል የፀለምትና የሰሜን ተራራዎች ይታያሉ፡፡ ሰማዩ አልፎ አልፎ ዳመና አዝሏል፡፡ ከበድ ያሉ ደመናዎች ወደ ራስ ዳሽንና ወደ ቧሂት ተራራ ሲጓዙ ከሩቅ ይታያሉ፡፡ በስተግራ በኩል የተንቤን ተራራዎችና የተንቤን በረሃ፣ እንዲሁም በቀኝ በኩል የአድዋ ተራራና እምባ ሶሎዳ ይታያሉ፡፡ ቁጭ እንዳልን

እነዚህን በሩቅና በቅርብ የሚታዩ የተፈጥሮ ፀጋዎችን እያየን ትንፋሽ ከወሰድን በኋላ ማውራት ጀመርን፡፡” (የአሲምባ ፍቅር፤ ገፅ 289)

በዚህ ውብ ቦታ የተቀመጡት ታጋይ ጥንዶች በፍርሃትና በናፍቆት፤ በትግልና በፍቅር መካከል ይዋልላሉ፡፡ ምክንያቱም ከአንድ ቀን በኋላ የውቅሮ ኦፕሬሽን ይካሄዳል፡፡ እዚያ ምን እንሚጠብቃቸው አያውቁም፡፡ እናም ዝምተኛው አማኑኤል ምንም ይሁን ምንም መቸም ይሁን የትም፤ እንደሚያፈቅራት እየደጋገመ ይነግራታል፡፡ ትግላቸው ከተሳካ በኋላ አብሯት ለመኖርም ቃል ይገባላታል፡፡ ድላይ ለፍቅራቸው ቃል ኪዳን ብትገባም፤ በትግል ወቅት አካሌ ሊጎድል ይችላል ብላ ብታቅማማም፤ የሆነውን በፀጋ ተቀበለች፡፡

አስቡት?.. ፍቅር መጀመራቸው በድርጅቱ ቢታወቅ ምን እንደሚያስከትልባቸው ያውቃሉ… ነገር ግን በእሳት መካከል ሆነው ነገን በማሰብ… በአላማና በፍቅር ፀንተው ዘመን ተሻግረው ያልማሉ፡፡ በዚህ ላይ ደግሞ በውቅሮው ኦፕሬሽን ላይ የሚሳተፈው የአማኑኤል ነገር ፍርሃት ፈጥሮባታል፡፡ እሱ የሚያውቃት ደግሞ በደፋርነቷ እንጅ በፍርሃቷ አይደለም፡፡

በነገራችን ላይ ድላይ ፍርሀትን የማታውቅ፤ በጀግንነቷ ለብዙ ታጋዮች አርአያ እንደ ነበረች ይነገርላታል፡፡ የድላይን ጀግንነት የሚያስታውሱት ታጋይ ገነት ታደሰ፤ ያልተዘመረላቸው፤ የኢህዴን/ ብአዴን እንስት ታጋዮች የትግልና የድል ታሪክ በሚለው መፅሀፋቸው ውስጥ እንደ ድላይ ዝነኛ ታጋይ የመሆን ህልም እንደ ነበራቸው አስነብበውናል፡፡

“በሪጅን ሶስት የበለሳው ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ አባል በመሆንና ኢህአፓን በመታገል ጉልህ ሚና ከነበራቸው ታጋዮች መካከል፤ ክቡር መስዋዕትነት የከፈለች፤ በምሳሌነት የምትጠቀሰው የኢህአሰ አባልና የሀይል 13 ምክትል ኮማንደር (የሃይል ም/አዛዥ) የነበረችው ጓዲት ድላይ ነበረች፡፡” (ያልተዘመረላቸው የኢህዴን/ብአዴን እንስት ታጋዮች የትግልና የድል ታሪክ፤ ገፅ 11)

ታሪኩ ከተፈፀመ ከ30 አመታት በኋላ ያችን ቅፅበት እንዲነግረኝ ደራሲውን ስጠይቀው ስሜቱ ተረባብሾ፤ ፈዞ እያስተዋለኝ ነበር፡፡

“አየህ?… ያን ጊዜ ያለወትሮዋ ፈርታ ነበር፡፡ እየደጋገመች ‘አማኑኤል? እኔ ግን ፈርቻለሁ! ድጋሚ የምንገናኝ ሁሉ አይመስለኝም’ ስትለኝ ነበር፡፡ ድላይ የምትታወቀው

ደፋር፣ ፍርሃት ያልፈጠረባት፣ ጀግና ታጋይ መሆኗ ነው፡፡ ያን እለት ግን ፈርታ አስፈራችኝ፡፡" ብሎኝ ዝም አለ፡፡ እኔ ግን ቀጠልሁ፡፡ ምክንያቱም የድላይ ንግግር ትንቢት ይመስል ነበር፡፡

"...አ...ዎ!... 'ለአንተና ለየአብዬ በጣም ፈርቻለሁ!... ድጋሚ በህይወት የማገኛችሁ አይመስለኝም!...' ብላኝ ነበር..." አለኝ፣ እንባ እየተናነቀው፡፡

ከመጥፎ ስሜቱ እስኪወጣ ድረስ ዝም ተባባልን፡፡ እኔ ግን የመፅሃፉ ታሪክ በእዝነ ልቦናዬ እየዋለለ ነበር፡፡ በማይ ምሻም ተራራ ብቻቸውን አምሽተው፣ ለብቻቸው ሲጫዋወቱ አድረው፣ በነጋታው ከሚካሄደው ጦርነት በኋላ፣ በሰላም ለመገናኘት የያዙትን ቀጠሮ አሰላስላለሁ፡፡ ነገር ግን ወደ መንደሩ ሲደርሱ መንገድ ላይ ሰራዊቱን ያገኙታል፡፡ የድላይ ጋንታ መሪ ወደ ቡድኗ እንድትቀላቀል ይነግራታል፡፡ ሁለቱም በድንጋጤ በድን ይሆናሉ፡፡

"ያላሰብነው ነበር፡፡ እ...ና... ስትለየኝ እጇን ለሰላምታ አውለበለበችልኝ... በቃ ተለያየን..." ሁነቱ አሁን የተፈፀመ ይመስል እጁን በዝግታ አንስቶ አወዛወዘው... ቻው! ቻው! እንደ ማለት

በነጋታው ማለዳ አማኑኤልና ሌሎች አመራሮች፣ ውቅሮን ለማጥቃት ከሚሄደው ሰራዊት በፊት ቀድመው መረጃ ሰበሰቡ፡፡ ደርግ ቀድሞ እንደተዘጋጀ ተነገራቸው፡፡ ሃይል መሪው ግን የበላይ ትዕዛዝ ስለሆነ ጦርነቱ መካሄድ እንዳለበትና መረጃው በሚስጥር እንዲያዝ አስጠንቅቆ ውጊያው እንዲካሄድ ይደረጋል፡፡

የድርጅቱ ከፍተኛ አመራሮች የደረሰውን መረጃ አውቀው ሳይወስኑ በተደረገው ውጊያ፣ እነየአቢን ጨምሮ የበርካታ ጎበዝ ታጋዮች ህይወት ተቀጠፈ፡፡ በዚህ ውጊያ ሽፋን ለመስጠት የእነድላይ ይመጣል፡፡ በተፈጠረው አሳዛኝ ሁኔታ እያዘኑ፣ ቁስለኞቻቸውን ይዘው ተመለሱ፡፡ ጓዶቻቸውን ተሸክመው የነበሩት ድላይና አማኑኤል በደም ተጨማልቀዋል፡፡ እናም ድጋሚ ልብሳቸውን ለማጠብ ወንዝ ወረዱ፡፡ ስለ ወደ ፊት የፍቅር ህይወታቸው አወጉ፡፡ ያም ሆኖ ግን የድላይ ትንቢት መሰል ፍርሃት እውነት ሆነ፡፡ ካህሳይ ወደ ሱዳን አቀና፡፡ ድላይ ወደ በለሳ ሄደች፡፡

ወራቶች ነጎዱ… አማኑኤል በስደት ካለበት ሱዳን ሆኖ ያስባታል… ድላይም ፍቅሯን በውስጧ ይዛ ትግሏን በበለሳ ቀጥላለች… በዚህ መካከል አማኑኤል ወደ ሀገረ አሜሪካ ተጓዘ… የካህሳይ ኩርባዎች ግን ቀጠሉ…

***የድላይ ትውስታ…***

ብዙ ያልተዘመረላት ታጋይ ድላይ፣ የኢህአፓን የተሳሳተ የትግል ስልት በመኮነን በተነሳው፣ የበለሳው ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ ውስጥ ንቁ ተሳታፊ እንደነበረች፣ ታጋይ ገነት ታደሰ በ2008 ዓ.ም ባሳተሙት፣ "ያልተዘመረላቸው፣ የኢህዴን/ ብአዴን እንስት ታጋዮች የትግልና የድል ታሪክ" በሚለው መፅሀፋቸው፣ በገፅ 11 ውስጥ ጠቅሰዋል፡፡

"…ድላይን በቅርብ አውቃታለሁ፡፡ የኢህአፓ አባል በነበርኩበት ወቅት ወታደራዊ ስልጠና ሰልጥኘ የተመደብሁት መጀመሪያ እሷ በምትመራው ሃይል 13 ነበር፡፡ ስለ ጀግንነቷ መመስከር እችላለሁ፡፡ እኔም በትግሉ ጠንካራ ተዋጊና አዋጊ መሆን የቻልሁት አንደኛው የድላይን አርአያ በመከተሌ ነው፡፡ 'በማንኛውም መስክ ጠንካራና አርአያ የሚሆን ሰው ካለ በርካታ ተከታዮች ይኖራሉ፡፡' የሚለውን ትክክለኛ አባባል ድላይ አስመስክራለች፡፡"

ታጋይ ድላይ በንቅናቄ ውስጥ እያለች ነበር፣ በ1972 ዓ.ም መጨረሻ በለሳ አካባቢ የተሰዋችው፡፡ በወቅቱ የሚያውቋት ታጋዮች የነበራትን ቆራጥነትና የጀግንነት ታሪክ፣ ዛሬም ድረስ ያስታውሱታል፡፡ ለዚህ አስረጅ የሚሆነን ደግሞ፣ በ2007 ዓ.ም "ታሪክና ጥበብ" በሚል ርዕስ፣ የትግል ግጥሞችን ለንባብ ያበቁት ታጋይ ህላዊ ዮሴፍ፣ ስለዚች ጀግና ታጋይ "እኔም እንዳንች ድል ላይ ልቁም" ሲሉ ለማስታወሻነት ያሰናዷት ስንኝ ትጠቀሳለች፡፡

*….የጠፋች መስላ የማትጠፋ፣*

*ቆይታ ውላ የምትፋፋ፣*

*አዝርዕት ሁሉ የሚሻሟት፣*

*ሰው እንስሳው የሚሞቃት፣*

*የማለዳ ፀሃይ ምስል፣*

*የማታ ፀሃይ ስዕል፣*

*የብሩህ ተስፋ ውጋገን፣*

*የድልየነፃነት ብርሃን......*

*.......ሀሊናዬም ይደንዝ፣*

*ዓይኔም ይጥፋ ይደብዝዝ፤*

*እጄም እግሬም ይዘርጋ፣*

*ልሳን አንደበቴም ይዘጋ፤*

*ሁለመናዬ ይጥፋ...*

*የልብ ትርታዬም...*

*እኔም እንዳንቺ ድል ላይ ልቁም፣*

*እኔም እንዳንቺ ድል ላይ ልቁም፡፡* (መጋቢት 1972 ዓ.ም በለሳ፤ ጎንደር)

"ባሰብሁሽ ቁጥር፣ ሁሌ እንደ ታናሽ ወንድምሽ፣ በቅፅል ስሜ ስታቆላምጭኝ ይታወሰኛል... ድላይ ከቆራጥ ታጋይነቷ በተጨማሪ ለትግል ጓዶቿ ፍቅርና ሩህሩህ ልብ የነበራት፤ ለህዝብም ታላቅ አክብሮት ትሰጥ የነበረች ታጋይ ነች፡፡" ይላሉ፤ ገጣሚው፡፡ (ታሪክና ጥበብ፤ ገፅ 56-57)

ከባለ ታሪኩና ከመፅሃፉ ደራሲ ከካህሳይ አብርሃ ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ የተገናኘነው በ2006 ዓ.ም መጨረሻ አካባቢ ነበር፡፡ በወቅቱ በመፅሃፉ ዙሪያ የሚካሄደውን የውይይት መድረክ የመምራት እድሉ ነበረኝ፡፡ ያኔ ታዲያ ከድላይ ጋር ስለ ነበረው የፍቅር ሁኔታ አንስቸለት ነበር፡፡ እንባው እየወረደ ታሪኩን በአጭሩ ተናገረ፡፡

"...በቃ... ድ..ላ...ይን... ዛሬም እወዳ...ታ..ለሁ!... አከብራ...ታለሁ... ጀግና... ታጋይ... ለዓላማዋ የተሰ...ዋች... ሁሌም... ቢሆን የማልረ...ሳት ናት..." ከዚህ በላይ መናገር አልቻለም፡፡ አዳራሹ ውስጥ የነበረው ታዳሚ በሀዘን ተዋጠ፡፡ ከመካከል ግን ጎላ ብሎ የሚሰማ የአንዲት ሴት ድምፅ ነበረ፡፡

አስቡት?... ከ30 ዓመታት በኋላም ድላይ ግዙፍ ነስታ በልቦናው ውስጥ ነግሳለች፡፡ የመጨረሻ እረፍቷን ለማወቅ ያልጠየቀበት፤ ያላስፈለገበት መንገድ አልነበረም፡፡ ከሚኖርበት ሀገረ አሜሪካ ተመልሶ ቤተሰቦቿን ሳይቀር አፈላልጓል፡፡ እናም አዳራሹ ውስጥ ምርር ብላ ስታለቅስ የነበረቸውን የድላይን እህት፤ ድርብ ምናለ ከ30 ዓመታት ፍለጋ

በኋላ ጎጃም፣ ቡሬ ከተማ ውስጥ አገኘች፡፡ እናም በመድረኩ ተገኝታ እንባዋን እየዘራች ሀሳቧን ተናገረች፡፡

"…የእህ…ቴን ታሪ…ክ እሰማ ነበር… ስሟና ታሪ…ኳ…ተጻ…ፍኖ በመቅረቱ አ..ዝን ነበር… ታሪኳ በመፅሃፍ ወጥ…ቷል ሲሉኝ… መፅሃ…ፉን ገዛቸ… ሶ..ስት ቀን አ..ቅ..ፌው ተ..ኛሁ… ዛሬ እ…ህ…ቴ አል..ሞተ..ችም!…"

"የአሲምባ ፍቅር" የተባለው መፅሃፍ የዚያን ትውልድ እውነተኛ የትግልና የፍቅር ታሪክ፣ ከራሱ ገጠመኝ በመነሳት የፃፈው ደራሲ ካህሳይ፣ እውነታውን ፍንትው አድርጎ ማሳየት በመቻሉ፣ በዚህ ዙሪያ ከተፃፉ መፅሃፎች የተለየ ያደርገዋል፡፡ ምክንያቱም የአሁኑ ትውልድ የዚያን ዘመን የትግልና የፍቅር የታሪክ እውነት እንዲገነዘብ ይረዳል ብዬ አምናለሁ፡፡ በዚህ ሀሳብ ላይ ደራሲ፣ ገጣሚና ጋዜጠኛ ነብይ መኮንን በመፅሃፉ ጀርባ የሰጠው አስተያየት ይጠቀሳል፡፡

"የኢትዮጵያን ህዝባዊ አቢዮታዊ ፓርቲን ታሪክና የትግል ጉዞ አስመልክተው ብዙ ሰዎች ፅፈው አንብቢያለሁ-በያገባኛል ባይነትም በታሪክ ንባብ ፍቅርም፡፡ ሁሉም የሚስማሙበት አንድ ፍሬ-ነገር፣ የኢህአፓ ታሪክም ሆነ የሌሎች ፓርቲዎች ታሪክ፣ በየአቅጣጫው መፃፍ አለበት የሚለው ይመስለኛል፡፡ በቃል ያለ ይረሳል፣ በፅሁፍ ያለ ይወረሳል ይሏልና፡፡"

በአጠቃላይ የዚያ ትውልድ የታሪክ እውነት በሚገባ ተፅፎ ለትውልዱ ተላልፏል ብዬ አላስብም፡፡ ይሁን እንጅ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ባለ ታሪኮቹ ታሪካቸውን እያስነበቡን ነው፡፡ ከእነዚህ ባለ ታሪኮች መካከል አንዱ ደግሞ ደራሲ ካህሳይ አብርሃ ይጠቀሳል፡፡ እኔም የመፅሃፉን ታሪክ መነሻ በማድረግ፣ ከደራሲው ጋር የነበረኝን ቆይታና የተለያዩ የታሪክ ድርሳናትን በማዛመድ በሶስት ክፍል ያደረግሁት የወፍ በረር ቅኝት በዚህ ተቋጨ፡፡